# ጥቂት ወንጌል

## በእጅዎ ያለዉ ወ<u>ንጌል</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የእግዚአብሔር ወንጌል | ሮሜ 1፥1 |
| 2. | የክርስቶስ ወንጌል | 2ኛ ቆሮ 2፥12 |
| 3. | የመንግስት ወንጌል | ማቴ 24፥ 14 |
| 4. | የፀጋ ወንጌል | የሐዋ 20፥24 |
| 5. | የሰላም ወንጌል | ኤፌ 6፥15 |
| 6. | የደህንነት ወንጌል | ኤፌ 1፥13 ፤ |
| | | 1ኛ ቆሮ 15፥1 |
| 7. | የክብር ወንጌል | 2ኛ ቆሮ 4፥4 |

*መሆኑን ያዉቃሉ ? ካወቁ ምን ያህል ጊዜ ያሰጡታል ? እርሱ ፥ በሰጡት ልክ ራሱን ይሰጥዎታልና ይበርቱ ፤ ያጥኑት ይመርምሩት ።*

*" ጥቂት ወንጌልም " ይህን ለማበረታታት ጥቂት እገዛን ለማድረግ ከጎንዎ መሆንዋ ይታወቅላት ዘንድ ጥረትዋ ነዉ ።*

*ታዲያ እኮ እርስዋ <u>መፅሐፍ ቅዱስዎን</u> አትተካም ፤ በ-ፍ-ፁ-ም !*

## *jyH፥|*

### *Odፍንት 12 mØ` 1-6*

*ምነዉ? ለምን አልጠራኸንም? አብረን ብንዋጋ አብረን የድሉ ባለቤት እንሆን አልነበረምን? ይህንን ባለማድረግህ ቤትህን በአንተ ላይ እናቃጥለዋለን ብለዉ የኤፍሬም ልጆች ወደ ዮፍታሄ መልእክተኞች ላኩበት።*

*ጠራኃችሁ ፥ እናንተ ግን አብራችሁኝ መሄድ ባልወደዳችሁ ጊዜ ነፍሴን በእጄ አድርጌ በአሞን ልጆች ላይ አለፍሁ፥ እግዚአብሄር በእጄ አሳልፎ ሰጣቸዉ ። በማለት የመለሰላቸዉ መልስ የኤፍሬም ልጆችን አስቆጥቷልና ጦር ተከተተ፤ ሰራዊት ዘመመ ፤ ሄደ*

*ስልትን የሚያዉቅ ጦረኛ፥ ምክርን የሚያዉቅ ጥበበኛ ተሰበሰበ መከረ ፥ አወጣ አወረደ ፥በላይ በታች ከበበ ፥ መተናፈሻ ጠፋ ዮፍታሄ በረታ ኤፍሬም ተሸነፈ፥ ሸሸ ።*

*ኤፍሬም የሚያልፍበት መንገድ በገለአዳዉያን ስለተያዘ መሹለኪያ ጠፋ። ፊት ለፊትም ጨክኖ የሄደዉን ኤፍሬማዊ የማለፊያ ፈተና ይጠብቀዉ ነበር።*

*ያዩአታል ! አሻግረዉ ምድራቸዉን ፥ የነፃነት ስፍራቸዉን ቢሄዱ ፤ ቢደርሱባት ፤ ቢረግጥዋት በህይወት እንደሚኖሩባት እርግጠኞች ናቸዉ ነገር ግን በእነርሱና በምድራቸዉ መካከል ገለአድ አለ ጥያቄና ጦር ይዞ የሚጠብቅ ፦ አንተ ኤፍሬማዊ ነህን ? ይላል መልሱ አይ ፤ በፍፁም ! ከሆነ እስቲ " ሽቦሌት " በል ?*

*ማንም ኤፍሬማዊ " ሽ " የምትለዋን ፊደል መጥራት ያስቸግረ ዋልና " ከሽቦሌት" ይልቅ " ሲቦሌት" ይቀናዋል ስለዚህም በዚያን ቀን ብቻ " ሽቦሌት "ብለዉ መናገር ባለመቻላቸዉ* 42.000 *ሰዎች ህይወታቸዉ እንዳለፈች ተመዝግቦልናል።*

*ከሞት ወደ ህይወት ማለፊያዉ ፤ መሸጋገርያዉ ብቸኛዉ መንገድ ኢየሱስ ጌታዬና አምላኬ ማለት ሲሆን " የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል " አወን ! ከሞት ወደ ሕይወት መሻገርያ ብቸኛ መንገድ ኢየሱስ ።*

*ይህ ኢየሱስ አለዎት ? ለዘላለም ሕይወት*
<u>*" ልጁ ያለዉ ሕይወት አለዉ ፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለዉ ሕይወት የለዉም "*</u> 1ኛ ዮሀንስ 5፥12

# በቁስሉ እናዉቀዋለን

" የኢየሱስ ሕይወት በሰዉነታችን እንዲገለጥ ፤ የኢየሱስን ሞት ዘወትር በሰዉነታችን ተሸክመን እንዞራለን ። "     2 ቆሮንቶስ 4÷10

ከትንሳኤ በኋላ ኢየሱስ ምን ይመስል ነበር ተብለዉ ቢጠየቁ መልስዎ ምን ይሆን ??

ተዉት አልፈርድብዎትም ፤ ምክንያቱም አብረዉት ለሶስት አመት ተከትል ያሳለፉት ደቀ መዛሙርት እንኳን ሊለዩት ባለመቻላቸዉ ሉቃስ 24÷37-39  መንፈስ ያዩ ስለመሰላቸዉ ኢየሱስ የሚለይበትን የእጆቹንና የእግሮቹን ቁስል ማሳየት ነበረበት ።

ኢየሱስ በዮሀንስ ወንጌል 20÷20 ላይም ከትንሳኤ በኋላ በቁስሉ ነበር ደቀመዛሙርቱ ያወቁት ። ታዲያ ለምን እግዚአብሄር አብ ከትንሳኤ በኋላ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በአዲስ አካል ፤ አለ ቁስል ከመሆን ይልቅ ከነቁስሉ ጠባሳ እንዲዘዋወር ፈቀደ ? ለምንስ ከነቁስሉ ወደገነት ሄደ ?

አስበዉበት ያዉቃሉ ??? ካልሆነ አሁን እስቲ አስቡበትና መልስን ለራስዎ ይስጡ ።     ለምን በቁስል ኢየሱስ ???? በጠባሳ !!!!

" የኢየሱስ ሕይወት በሰዉነታችን እንዲገለጥ ፤ የኢየሱስን ሞት ዘወትር በሰዉነታችን ተሸክመን እንዞራለን ። " ማለት ፥ ያንን ኢየሱስ በሞቱ ያገኘዉን ጠባሳ ዛሬ እኛ በምድር ይዘነዉ እንዞራለን ማለቱ ነዉ ??     ምን ይመስልዎታል ?

# አ-ይ-ገ-ድ-ህ-ም-ን-?

ሉቃስ 10÷40

የምስራቹን ወንጌል እየሰበከ ህዝብን ከደዌዉና ከህማሙ እየፈወሰ በመዘዋወር ማርታና ማርያም ወደ ነበሩበት መንደር በመጣ ጊዜ ማርታ በቤትዋ ተቀበለችዉ።

ኢየሱስ ማራታና ማርያም ቤት እንደደረሰ ማርታ አገልግሎት እንደበዛባት ማንበባችን፥ የሚበላ ወይም የሚጠጣ ለማዘጋጀት እየሞከረች ይሆናል ብለን እንድንገምት ሲያደርገን፤እህትዋ ማርያም ግን ቃሉን ለመስማት በእግሩ አጠገብ መቀመጥዋ ለማርታ ልትቀበለዉ ያልቻለችዉ ነገር ስለሆነባት ይመስላል አ-ይ-ገ-ድ-ህ-ም-ን-?  ለማለት ያስደፈራት።

የንባብ ክፍል

ሉቃስ 10÷38-42

አ-ይ-ገ-ድ-ህ-ም-ን-?   ማርያም እንደ እኔ መሆን ሲያቅታት አይገድህምን ? እህቴ ብቻዬን ስትተወኝ ? አ-ይ-ገ-ድ-ህ-ም-ን-? ። ማርታ፥ ማርያም ልክ እንደ እርስዋ እንድትሆንላት የቻለችዉን ሁሉ ጥረት ስታደርግ አምላካዊ መልስ ግን ትጨነቂአለሽ፥ትታወኪማለሽ ግን ለምን ? ለምን ? ማርታ ! ለምን አንደዚህ ትሆኛለሽ? ነበር።

ምናልባት ዛሬ ጥረታችን በቤት ቢሆን በቤተ ክርስቲያናችን ሁሉም እኛን እንዲመስሉ ፥ እንደ እኛ እንዲያስቡ ፥ እንዲናገሩ፥እንዲራመዱ ፥ አንዲያገለግሉ ፤ ሲሆን ለዚህ የምናጠፋዉም ጊዜና ጉልበት ይህ ነዉ የማይባል ነዉ።

የሁላችንም ፀሎት አ-ይ-ገ-ድ-ህ-ም-ን-? አንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባል ምክንያቱም "የፀጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነዉና አገልግሎትም እንዲሁ ልዩ ልዩ ነዉና "1ቆሮ 12÷4  ልዩነታችን ዉበታችን ነዉና ማርያም፥ ማርያም ትሁን እንተዋት የተሻለ መርጣለችና ።

" ሁሉም አንድ ብልት ቢሆንስ አካል ወዴት በሆነ? "1ቆሮ 12÷19

# እስከ መቼ ነዉ

## አንደኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 1÷14

ከዚህ በፊት አድርጌዋለሁ ፤ ሞክሬዋለሁ ፤ አልሆነም አልሰራልኝም :: አልቅሻለሁ ፤ ሰዉነቴንም ከምግብ ከልክያለሁ አልሆነም ፤ አልሰመረም ::

እገኛለሁ ባለበት ፤ ክብሩ በሰፈነበት ፤ ቤተ መቅደሱ ፤ እዛ እሄዳለሁ ፤ አነባለሁ ፤ እጮሀለሁ ፤ ከአሁን በኋላ በሰዉ ፊት አላለቅስም ገበናየን እሰዉራለሁ ፤ እሸሸጋለሁ ÷ ለእርሱ ለአምላኬ ብቻ እገልፀዋለሁ ::

ወደ ቤተ መቅደስ ሄዳ የልብዋን ብሶት በእሪታ ለአምላክዋ ሉ ! አለች ጮኋች ፤ ፊቱን ሻተች ፤ ክንዱን ናፈቀች ፤ ፍሬን ለመነች ሀና ::

ቁጭ ያለዉ ካህን (ኤሊ) ያልሰማዉ ፤ ምንም ያላደመጠዉ ፤ ወቀሳት ፤ ገሰፃት ፤ ዘለፋት ፤ ከሰሳት“ ስካርሽ እስከ መቼ ነዉ ?” የወይን ጠጅሽን ካንቺ አርቂዉ ተባለች ፤ በመቅደስ ተወነጀለች :: ድምፅዋ ባለመሰማቱ ተዘለፈች ፤ ተወቀሰች ፤ ተገሰፀች ::

ሊቆጣጠሩት አልቻሉም ፤ ከአቅም በላይ ነዉና ፤ ሊይዙትም አስቸገራቸዉ ሀይል ነዉና ፤ ለቀቁት ይሂድ አሉት ÷ ተናገሩ ፤ ጮሁ ህዝብ ሰማ አለም አደመጠ ፤ ተደነቀ ፤ የራሱን ቋንቋ ሰምቷልና ዋዉ ! አለ ::

ምነዉ በማለዳ አሉ ሌሎች ፤ ተደነቁ አንዳንዶች ፤ መዘኑ አዩትና አፌዙባቸዉ ፤ ከግምት በታች አደረጉአቸዉ ሰ-ካ-ራ-ም- “ ጉሽ ወይን ጠጅ ጠግበዋል ” ተባሉ ፤ ተወቀሱ በባለ ሀምሳ መንፈስ ሲወርድባቸዉ ::

> <u>ንባብ</u>
> የሐዋ 2÷1-13

የትኛዉ ነዉ የሚሻለዉ ? የሚስማማዉ ? ነቀፌታን የማያስከትለዉ ? ንገረኝ እሰማለሁ ፤ አስተምረኝ እማራለሁ :: ግን ዝም ብለህ አትዉቀሰኝ ፤ አትገስፀኝ እኔምኮ እለወጣለሁ ፤ ካስረዳኸኝ እረዳለሁ ፤ ካስተማርከኝ እማራለሁ

የትኛዉ ነዉ ትክክሉ ? ለሁላችን የሚበጀዉ ? የሚጠቅመዉ ? እርሱን እናድርግ እንስማማ :: ግን አትበለኝ እ-ስ-ከ-መ-ቼ ::

# ከበዉት ሳሉ

## የሐዋርያት ስራ 14÷19-20

ከእናቱ ማህፀን ጀምሩ እግሩ የሰለለ አንካሳ ሰዉን ፤ ጳዉሎስ በልስጥራን አገልግሎቱ “ ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም ” ብሎ በመናገር ከተፈወሰ በኋላ እንደ አማልክት ክብርን ወዲያዉ በመስጠትና ስማቸዉን ሳይቀር በመለወጥ አግባብ ያልሆነ ሞገስን ስለሰጡአቸዉ ጳዉሎስ በመጮህ ነበር ያስቆማቸዉ ::

ይህ ታላቅ የሆነ አክብሮት ወዲያዉ በመለወጥ ቡጢን አስከትሎ ጳዉሎስን ከወገሩት በኋላ እነርሱ ሞቶአል ብለዉ ባሉበት ጊዜና ሁኔታ ላይ ሰዉ እንኳን እንዳይቀብረዉ ከከተማ ዉጭ አዉጥተዉ ጣሉት::

በቁስል ፤ በደም ተነክሮ ዉበት ባጣበት ጊዜ ፤ በዛን ጊዜ ነበር ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ በመምጣት ከበዉት የቆሙት ፤ ምንም አላደረጉም ነገር ግን ከበዉት ብቻ ቆሙ ::

> <u>ንባብ</u>
> <u>የሐዋ 14÷8-20</u>

ለየት ያለ መቆም እንጂ እንደ ማንኛዉም ጊዜ ወንድሞችን ከበን የምንቆመዉ መቆም አይመስልም :: ማንም ምንም አላለም ፤ እንደዉ ዝም ብለዉ ቆሙ ከበዉት ፤ ዙሪያዉን አጥረዉት ፤ አጋር ከለላ ሆነዉት

ሞተ የተባለዉ ሰዉ መነሳቱን ብቻ አይደለም የተፃፈልን ወደ ከተማም መግባቱ ጭምር ነዉ :: ከሕዝብ መቀላቀሉ ምንም የተደረገለት ነገር አልነበረም ፤ ማንም እጁን ይዞ አላነሳዉም ቁጥር 20 “ደቀ መዛሙርቱ ግን ከበዉት ሳሉ ተነስቶ ወደ ከተማ ገባ ” ዝም ብለዉ ከበዉት ሳሉ :--ተነሳ ! ወደ ከተማም ገባ ::

የእርስዎ መገኘት :-የደከመዉን ከድካሙ ፤ የወደቀዉን ከዉድቀቱ አንስቶ ከሕዝብ ይቀላቅለዋል ÷ በወንድሞች መካከል መገኘትዎ ለሌሎች በረከትን ያመጣል ? የሞተባቸዉን ሕያዉ ያደርጋል ፤ ስለ ራስዎ ምን ይላሉ ????? **ሀቁን** !!!!!

ኢሳያስ 40÷1 “ አፅነኑ ሕዝቤን አፅናኑ ይላል አምላካችሁ ”

# <u>ምን እጠቅማችኋለሁ ?</u>

1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 14 ÷ 6

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከማንኛዉም የአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት በበለጠ ሁኔታ የፀጋ ስጦታዎች የነበሩዋትና ልምምዱም ይታይባት የነበረች ብትሆንም ሐዋርያዉ ጳዉሎስ በመልዕክቱ 14 ቁጥር 1 “ መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ ፈልጉ ” በማለት ያደፋፍራቸዋል ፡፡

ይሄ ጉጉት በእናንተ ዉስጥ ካለ የምመክራችሁ ነገር አለኝ እባካችሁ ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ ትንቢትን የሚናገር ህዝብን ለማነፅ ፤ ለመምከር ፤ ለማፅናናትም ለሰዉ ይናገራልና ( 14 ÷ 3 )

“ በልሳን የሚናገር ግን ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰዉ አይናገርምና የሚያስተዉለዉም ማለት የሚረዳዉም የለምና ” ( 14 ÷ 2 ) ወንድሞችና እህቶች ይታነፁበት ፤ ይመከሩበትና ይታነፁበት ዘንድ ትንቢትን እንድትናገሩ በብርቱ ፈልጉ ፡፡

እስቲ ተመልከቱ “ ወደ እናንተ ጉባኤ መጥቼ በልሳን ብናገራችሁ በመግለጥ ወይም በእዉቀት ወይም በትንቢት ወይም በትምህርት ካልነገርኋችሁ <u>ምን እጠቅማችኋለሁ</u> ? እንደዉም ከእናንተ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁና እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ፡፡ ነገር ግን ሌሎቹን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማሕበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ ፡፡ ” ( 14 ÷ 18 )

መሰብሰባችን እኮ ለመጠቃቀም ነዉ ፡፡ ልሳን ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርያ ነዉ እንጂ ከሰዉ አይደለምና አትሰሙኝም ስለዚህም ማንኛችሁም አሜን አትሉበትም ፡፡ አትታነፁበትም ፤ አትመከሩበትም አትፅናኑበትምም ÷ ሌሎችም አብደዋል እንዳይሉን በተገለፀዉ በሚያንፀዉ ፤ በሚያፅናናዉ ቃል እንጠቃቀም  አይመስልዎትም ??

# የሚመክር ቃል

የሃዋርያት ስራ 13÷15

“ህግና ነብያትም ከተነበቡ በኃላ የምኩራብ አለቆች ፡-ወንድሞች ሆይ ÷ህዝብን የሚመክር ቃል እንዳላችሁ ተናገሩ ብለዉ ላኩባቸዉ፡፡”

ዉብ በሆነች ማለዳ ፤ ሰማዩ ገና ሲፈካ ፤ ጥዋት ሲነሱ ጥሩ ስሜት ጨብጠዉ ወኔ ድፍረት ተሞልተዉ ፤ በቀኑ ዉበት ተደንቀዉ ጌታን እያመሰገኑ ቁርስ ቢጤ ቆራርሰዉ ለምስጋና ÷ለአምልኮና ለወንድሞች ሕብረት ወደ አጥቢያዎ ቤተ-ክርስቲያን ሲያመሩ ፤ ልብዎ ልዩ ምት ሲመታ በቀኝ በግራ ያለዉን ሰላም ሲሉ የፊትዎ ገፅታ ጎልቶ እየታየ

አምልኮ ተጀምሮ ህዝብ ግጥም ብሎ ሲደርሱ ፤ እንደ ምንም እንደዉ እንደ ምንም ቦታ አግኝተዉ ቁጭ ፤ ግራና ቀኝዎን ገልመጥ ገልመጥ አድርገዉ ገና ሳይጨርሱ በማጉያዉ መሳርያ ድንገት ስምዎ ቢጠራ ሰዉነትዎን የሚወረዉን ወረርሽኝ አልጠይቅዎትም ይቅር፤ ነገር ግን በስምዎ መጠራት መደናገርዎን ሳይጨርሱ“ ህዝብን የሚመክር ቃል እንዳለዎ ይናገሩ ” ቢባሉ በምእመናኑ ፊት ቢጠየቁ የህዝቡ ሁሉ አይን እርስዎን እያየ ሳለ ምላሽዎ ምን ይሆን ብዬ ብጠይቅዎ ምን ይላሉ??

ጳዉሎስና ጓደኞቹ የደረሰባቸዉ ይህን መሰል ገጠመኝ ነበር ፡፡ ለአምልኮ  ቤተ መቅደስ ሄደዉ በህዝብ መሀል“ ወንድሞች ሆይ ህዝብን የሚመክር ቃል ” ካላችሁ ተናገሩ ተባሉ ይህ ለርስዎ ቢሆን ምን ይላሉ?

“ ህዝብን የሚመክር ቃል ” ነዉ እንጂ ዝም ብሎ ቃል ብቻ የሆነ ቃል አይደለም ፡፡ እርሱንም ደግሞ ካላችሁ ነዉ የተባሉት ፤ አወን ህዝብን የሚመክር ቃል ካላችሁ ተናገሩ ÷   ከሌላችሁሳ?  ዝ-ዝ-ዝ-ም

ጳዉሎስና ጓደኞቹ በእርግጥም ህዝብን የሚመክር ቃልን አቅርበዋልና እባካችሁ በሚመጣዉም ሳምንት ቃል አምጡልን ተባሉ እርስዎ መቼ ነዉ ለመጨረሻ ጊዜ ህዝብን የሚመክር ቃል እንዳለዎ ተናገሩ የተባሉትና በእርግጥም ህዝብን የሚመክር ቃል ያቀረቡት ??

በእግዚአብሔር የተመከረ ነዉ የሚመክር እንጂ ፤ የመድረክ እድል የተሰጠዉ ሁሉ ህዝብን የሚመክር ቃል የለዉም፡፡ አይመስልዎትም ??

# ሁሉም ተዉኝ

## ሁለተኛ ጢሞትዮስ ምእራፍ 4 ቁጥር 16-17

"በፊተኛዉ ሙግቴ አንድ እንኳን አልደረሰልኝም ሁሉም ተዉኝ እንጂ ::ይህንንም አይቁጠርባቸዉ ዳሩ ግን የስብከቱ ስራ በእኔ እንዲፈፀም አህዛብም ሁሉ እንዲሰሙት ጌታ በእኔ አጠገብ ሆኖ አበረታኝ::"

ሀዋርያዉ ጳዉሎስ " ሁሉም ተዉኝ " ሲል ፊቱ በሀዘን ቅጭም ብሎ አይኖቹም እንባን አቅርረዉ ባዶነት ብቸኝነት ነግሶበት ከእርሱ ሩቅ ሳለዉ ለጢሞትዮስ የልቡን ለማካፈል ብቸኛ ሰዉ ያገኘ በሚመስል ስሜት ነበር::

"ሁሉም ተዉኝ" ሰዉ በፈለግሁ ጊዜ÷ አጋር በሻትሁ ጊዜ÷ አብሮኝ የሚቆም በተመኘሁ ጊዜ÷ አጠገቤ ሰዉ ጠፋ:: ዋ ! ዉ ! ሙግት ላይ በነበርኩ ጊዜ÷ ተቃዋሚዩ በላዩ በተነሳ ጊዜ ÷ሊዉጠኝ አፉን በከፈተ ጊዜ÷ በዛን ጊዜ አጋር በሻትሁ ጊዜ"ሁሉም ተዉኝ"

ጌታ ኢየሱስን ከ 5000 ሰዎች በላይ በመልካሙ ሰአት ተከተሉት ነገር ግን በችግሩ ሰአት ሰዉ በሚያስፈልግበት ሰአት ሁሉም ሸሹት" ሁሉም ተዉት " ለእርሱም ያ ስሜት ተሰምቶታል ያ ሁኔታ ደርሶበታል ጓደኞቹ ትተዉታል አጋሮቹ ርቀዉታል::

ሀዋርያዉ ÷ ጌታ ግን ከጎኔ ሆኖ አበረታኝ ይለናል አወን ሁነኛ ሰዉ በፈለግን ጊዜ ፤ ብቸኝነት በከበበን ጊዜ የዛን ጊዜ የእምነትን መዞር ዘወር እንበል፤ ጌታ በእርግጥ ከጎናችን ሆኖ እናየዋለንና::

አልተዉህም ከቶም አልለቅህም ያለዉ እርሱ ራሱ ነዉና በእርሱ እንበርታ ሁሉም ቢተዉን÷ የቀረብናቸዉ ቢርቁን ÷ የወደድናቸዉ ቢጠሉን÷ እምኞታችን ባንደርስ ፤ ባይሆን ባይሳካልን ጌታ አለ ከጎናችን እርሱ በኛ መልካምን ስራ ስለጀመረ ሳይፈፅመዉ አይቀርምና እንበርታ ::

የንባብ ክፍል
ፊሊፕ 1÷6

# አወን !

## እግዚአብሔር ጌታን አንዳስነሳዉ ፤ እኛንም ያስነሳናል ::

## 1ቆሮንቶስ 6÷14

ያንብቡ
ማርቆስ 16÷1-2

ከዛ ከጫጫታ ምሽት በኋላ ፤ ከዛ ዋይታና እንባ ከሞላዉ ምሽት በኋላ ፤ ሰንበት ካለፈ በኋላ ፤ ሰማያት ገና ሲፈኩ ምድር በብርሀን ስትዋብ ፤ ፀጥ ባለዉ ማለዳ ማርያም መግደላዊት በኢየሩሳሌም መንገድ ወደ ጎልጎታ በሚወስደዉ ጎዳና ወደ ዉድዋ መቃብር ስፍራ ከሌሎች ጋር ስታመራ ሽቱዋን ለፍቅረኛዋ ይዛ

ማርያም ቀድማ ደረሰች ፤ የማለዳዉ ፀሀይ ገና ሲወጣ ምድር ገና ፀጥ ባለበት ፍጥረት መላወስ ባልጀመረበት ÷ ዝም ፤ ፀጥ ፤ እረጭ

ድንጋዩ ወደ ጎን ተንከባሎአል ፤ ባለፈዉ አርብ እንዳየችዉ አይደለም :: ሮጠች ፤ ሄደች ፤ ገባች :: አወን ! ያልጠበቀችዉ ነገር ነዉ የሆነዉ የጌታ አስከሬን የለም ::ቃኘች ዙሪያዉን ፤ የከፈኑ ጨርቅ በጥግ አለ የጌታ ገላ ግን አልነበረም ፤ ወጣች ሄደች ነገረች ለሌሎቹ ሴቶች:: ሄደች ፤ ሮጠች ለጴጥሮስና ለዮሀንስ ነገረች :: " ዮሀንስ 20 ÷2 "

ወጣቱ (ዮሀንስ) ቀደመ ፤ ሄደ ፤ ገሰገሰ እመቃብሩ ደጃፍ ደረሰ ቆመ ÷ ጴጥሮስ ደረሰ ገባ ፤ ቃኘ ፤ አየ የጌታ አስከሬን በእዉነትም የለም :: ተመለሱ ለሌሎች ለመንገር ::ማርያም ቀረች በእንባ ፤ በሀዘን እመቃብሩ ደጃፍ ፤ ማመን ተቸገረች ዉድዋን ማን ወስዶት ይሆን ?

" አንቺ ሴት ስለምን ታለቅሻለሽ ?" አታክልት ጠባቂ መሰላት አልጠበቀችም ፤ አልገመተችም ፤ አላወቀችም ገና ስምዋ ሲጠራ ማ-ር-ያ-ም ! አወቀችዉ ጌታዋ ነዉ ፤ ለየችዉ አምላክዋ ነዉ :: ሊነገር የማይችል ደስታ ፤ ሄደች እግሩ ስር ወደቀች ፤ ወደደች ልትይዘዉ ልታቅፈዉ :: ኢየሱስ አልተሰረቀም ተነስቶአል !!!!!

ስምዋ ሲጠራ በአምላክዋ ማርያም ዘለለች ፤ ልዩ ደስታን ፈጠረባት ፤ ዉስጥዋን ስሜትዋን ነካት ልትቆጣጠረዉ አልቻለችም ተስፋ ያለዉ ማለዳ ፤ የትንሳኤዉ ማለዳ ፤ ጌታ የተነሳበት ማለዳ :: ተነስቶአልና ባለተስፋዎች ነን ፤ አርጓልና ሀገር አለን እ-ን-ፅ-ና-ና !!

# ትዉዉቅ

ስለሙዚቃ ሲነሳ ፤ በቅርብ ከእኛ ጋር ያሉ ፥ በአካል ተለይተዉን በአክብሮት ትዉስታቸዉ ለዘለአለም አብሮን የሚኖረዉን በዜማ ቅንብር መስጠታቸዉን እለት እለት የምናደንቃቸዉ አያሌ ወንድሞችና እህቶች ትዝ ይሉናል ::     እርስዎ ማንን አስታወሱ ?

መዝሙረኛዉ ዳዊትን ፤ ወይም ባለ ቅኔዉን ልጁን ሰለሞንን ማን መጣ ወደ አዕምሮዎ ? ሞዛርት ? ፤ ጉድ ማን ?     ማነዉ  ወደ አዕምሮዎ  ፈጥኖ የመጣዉ ? ያሬድ ?  ማነዉ?

ምናልባት   አሳፍ  የተባለዉን በዜማ ቅንብርና ዉበት በምክርና ትምህርት በዘመኑና ከዘመኑም በኋላ  ታላቅ አክብሮትን በማትረፉ ተወዳጅነትንና ክብረትን በመስጠት አለም ያከበረዉን ተወዳጅ አልጠቀሱ ይሆናል ?

አሳፍ :- መፅሀፍ ቅዱሳችን በመጀመሪያ ስሙን ሲጠቅሰዉ 1ዜና 6፥33-39  የስመ ጥር  መዘምራን ረዳት በመሆን ሲሆን የሰራዊትን ጌታ የእግዚአብሔርን ታቦት በማጀብ መዝሙራትን ከሚያሰሙትና አምልኮዉን ከሚመሩት አንዱ ነበር ::

የዜማ ቅንብሩ ፤ ምን ያህል ዉበትና ሀይል ቢኖረዉ ይሆን ንጉስ ዳዊትን እንኳን ክብሩን ትቶ በአደባባይ በሕዝቡና በእግዚአብሔር ፊት እንዲያ እንዲዘል ያደረገዉ ?

ያስታዉሳሉ ? የቃል ኪዳኑ ታቦት ለመጀመሪያ ጊዜ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ  የናስ ፀናፅል በመያዝ ድምፃቸዉን ከፍ በማድረግ ያሰሙ  ከነበሩት አንዱ እንደነበር -----(1ዜና 15፥19)

ብዙም ሳይቆይ በዚሁ በ1ዜና 16፥5 ላይ አሳፍ የዚሁ አገልግሎት መሪ ወይም አለቃ እንደተደረገና ንጉስ ዳዊትም በቁጥር 7 ላይ የደረሰዉን ዜማ ለአሳፍ እንደሰጠዉ ማንበባችን የአሳፍን የተዋጣለት የዜማ ሰዉ መሆኑን እርግጠኞች ያደርገናል ::

አሳፍ ለረጅም ዘመን የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ሁሉን ቻይነት ከወንድሞቹና ከሌሎች በዚህ ፀጋ ከተሞሉት ወገኖች ጋር 1ዜና 25 ፥ 1 ሲያገለግል ፤ ቁጥራቸዉም 288 እንደደረሰ 25፥7 ላይ ስናነብ እነዚህም እግዚአብሔርን ለማመስገን የሚያዉቁ ነበሩ ይለናል::

አሳፍ በዜማ ሞያ የተካነዉ በእርሱ ዘመን ብቻ ሳይሆን እርሱ ካለፈ በመቶዎቹ በሚቆጠሩ አመታት በኋላ 14ኛዉ የይሁዳ ንጉስ ሕዝቅያስ (2ዜና 29፥30 )ለመዘምራኑ በዳዊትና በባለራዕዩ በአሳፍ ቃል እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ዘንድ ትእዛዝን ሲሰጥማየታችን አሳፍ በእርግጥም የእግዚአብሔር ፀጋ በላዩ የነበረ አገልግሎቱም በእርግጥ አገልግሎቱ ነበር ያሰኘናል ::

መፅሀፍ ቅዱሳችን በመዝሙራቱ ዉስጥ አያሌ የሆኑ የአሳፍ መዝሙራትን ያቀፈ ሲሆን መዝሙር (50) ፤ (73-78) የአሳፍ መዝሙራት ሲሆኑ 74፤79 ና 80 ከዘመናት በኋላ በእርሱ ዝርያዎች እንደተፃፉ እናነባለን ::

አሳፍ :- ምን ያደርግልኛል ? ምንስ ይጠቅመኛል ? ካለህ ሌላ ፃፍልን ? ይሉ  ይሆን ??????????????????

መዝሙር (78) ፥3 ጀምረን  እናንብብ

የሰማነዉን ያወቅነዉን
አባቶቻችንም የነገሩንን
ለሚመጣ ትዉልድ ከልጆቻቸዉ አልሰወሩም ::
የእግዚአብሔርን ምስጋናና ሀይሉን ፥
ያደረገዉንም ተአምራት ተናገሩ ::

ቁጥር 6

የሚመጣ ትዉልድ ፤ የሚወለዱም ልጆች ያዉቁ ዘንድ ፥
ተነስተዉ ለልጆቻቸዉ ይነግራሉ ፤
ተስፋቸዉን በእግዚአብሔር እንዲያደርጉ
የእግዚአብሔርንም ስራ እንዳይረሱ

አሳፍ :- ዛሬ ለእኛ ፥ ተስፋችን በአምላካችን እንዲሆን ከዘመናት በፊት እርሱም ከአባቶቹ የተቀበለዉን ለእኛ አሳለፈልን እርስዎስ ተቀብለዉታል ?   ለማንስ እያሳለፉት ነዉ ?

ዛሬስ የእርስዎ ተስፋ ማን ነዉ ?      ይህ የአሳፍ ጥያቄ ነዉ

**ተስፋዎ ማን ነዉ ????**

የእግዚአብሔርስ ስራ ፤ ያደረገዉ በጎነት በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠዎት ልጅነት  ዛሬም በልብዎ ትኩስ  ነዉን ???

የዚህ ዘመን አሳፍ እርስዎ እንደሆኑ ማን ያዉቃል ??????